# ላለመደናገር . . .

# ማወዳደር

# ማሰላሰል

# ማጠቃለል

ገርሃርድ ኔልስ

# ትስማማለህን?

የራሳችንን አመለካከት የማይቀበለውን ሰው አብዝተው ከሚጎዱና ከተለመዱ የክርክር ልውውጦች ይልቅ የተሻለ የአቀራረብ ዘዴ መፈለግ አለበት።

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ተቃቅረው ሰንብተዋል። ከሚለያዩዋቸው ነጥቦች መካከልም የየራሳቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ከመለኮታዊ ምንጭ መምጣታቸውና እንደየእምነታቸው ለኢየሱስ ወይም ለመሐመድ የሚሰጡት ሥፍራ አጠያያቂነት ይገኙባቸዋል። ስለዚህ የእያንዳንዱ እምነት ተከታዮች የመከራከሪያ ነጥቦችንና መርሆአቸውን ማስደገፊያ ምርኩዝ መፈለጋቸው አዘውትሮ የሚስተዋል ጉዳይ ነው።

ክርስቲያኖች በመጽሐፋቸው ላይ ስለሚደርሱት በርካታ ጎጂ ጥቃቶችና በኢየሱስ ላይ ስለሚሰነዘሩት የተወሰኑ እስላማዊ አሳቦች ግራ ይጋባሉ። በመሆኑም የታሪኩን ሌላ ገጽታ ለማሳወቅ ሙስሊሞቹ እንዲያደምጡዋቸው ከልባቸው አጥብቀው ይሻሉ።

መንፈሳዊና እውነተኛ የሆነ ሰው የራሱን ወግ ተቀብሎ ታማኝነትን ማሳየት ብቻ ሳይሆን፥ አድልዎ በሌለበት ሁኔታ የሌላውንም ለማድመጥ የተዘጋጀ ነው።

# ቁርዓን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

«በአላህና ወደ እኛ በተወረደው (ቁርዓን)፥ ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም፥ ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው፥ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፥ በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከእነርሱ በአንዱም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን ...በሉ።» (ሱረቱ በቀራህ 2፡136)

«አላህ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ (እርሱ) ሕያው፥ ሁሉን ነገር አስተናባሪ ነው፤ ከእርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን፥ መጽሐፉን (ቁርዓንን) በአንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ። ተውራትንና (የሙሴ) ኢንጂልንም (የኢየሱስ) አውርዷል።» (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡2-3)

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልእክተኛው በዚያም በመልእክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ።» (ሱረቱ አል-ኒሳእ 4፡136)

«እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፤ ...አላህም ባወረደው

ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሐዲዎቹ እነርሱ ናቸው። ...የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራቱ በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን፤ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲሆን ሰጠነው። የኢንጂልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፤ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው።...አላህ ባወረደው ሕግ ፍርድ፤ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል። (ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡44፥46፥47፥48)

«እናንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁም ወደ እናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው» (ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡68)

«ይህ ቁርአን... ያንን ከእርሱ በፊት ያለውን የሚያረጋግጥ...ነው» (ሱረቱ ዩኑስ 10፡37)።

«ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፤ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ



በእርግጥ መጥቶልሃል፤ ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን።» (ሱረቱ ዩኑስ 10፡94)

«የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ... በሉም፡- በዚያ ወደ እኛ በተወረደው ወደ እናንተም በተወረደው አመንን።» (ሱረቱ አል-ሆንከቡት 29፡46)

«ይህም ያወረድነው የሆነ ብሩክ፥ ያንንም በፊት የነበረውን (መጽሐፍ) አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው፤ የከተሞችን እናት (መካን)ና በዙሪያዋ ያሉትንም ሰዎች ልታስጠነቅቅ (አወረድነው)» (ሱረቱ አል-አንዓም 6፡92)

አለ ጥርጥር ይህ ማለት መሐመድ የመጣው ለመካና ለዐረቦች ራእይን ለማድረስ ነው ለማለት ይቻላል። ይኸውም ከእርሱ በፊት የመጣውን (ራእይ) ለማጠናከርና ለማጽናት መሆኑ ነው።

«ከአንተም በፊት ወደ እነርሱ የምናወርድላቸው የሆኑ ሰዎችን እንጂ ሌላን አላክንም፤ የማታውቁም ብትሆኑ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ።» (ሱረቱ አል-አንቢያ 21፡7)

ከዚህ ላይ ቁርዓን «የመጽሐፉን» መለኮታዊ መገለጽና በነቢዩ መሐመድ ዘመንም ያልተበላሸ ይዘት እንዳለው

አድርጎ እንደሚያቀርብ በግልጽ ለማየት እንችላለን። ይሁንና ቁርዓን ማጣመምንና የአተረጓጎም ደጎነትን እንደሚከለተለው አጥብቆ ያወግዛል።

«የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሸት ለምን ትቀላቅላላችሁ? እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትሆኑ ለምን ትደብቃላችሁ?» (ሱረቱ አል-ዒምራን 3፡71)

«ከእነርሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲሆን ከመጽሐፉ መሆኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ።» (ሱረቱ አል-ዒምራን 3፡78)

እንግዲህ ከዚህ ጎልቶ የሚወጣ ነገር ቢኖር ቶራ (ሕግ) እና ወንጌል ሁለቱም ከእግዚአብሔር የመጡ ራእዮች መሆናቸው ነው። ይህ ደግሞ ክርስቲያኖችም የሚያምኑበት ጉዳይ ነው። ቁርዓንም ከእዚህ ላይ አክሎ ሲያብራራ እንዲህ ይላል፡-

«የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም።» (ሱረቱ ዩኑስ 10፡64)

«የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም።» (ሱረቱ አንዓም 6፡34)



«ከመልእክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አልላክንም፤ ባነበበ (ና ዝም ባለ) ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጂ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፤ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል፤ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።» (ሱረቱ አል-ሐጅ 22፡52)።

ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ከመሠረታዊ ይዘቱ አንዳች ለውጥ አድርጓል ብሎ እንዳይከራከር ታሪክና የከርሰ-ምድር ምርምር ቋሚ ምስክር ሆነው ይከለክላሉ።

መሐመድ ስለ «መጽሐፉ» ወይም «ተውራት»፥ «ዘቡር» ወይም «ኢንጂል» በጠቀሰ ጊዜ፥ በዘመኑ በዐረብ አገሮች ውስጥ ተሰራጭተው ስለነበሩት መጻሕፍት መናገሩ እንደነበር ጥርጥር የለውም። እንዲያው ለቃላት ትኩረት የምንሰጥ ከሆነ ደግሞ መሐመድ ይህን «መጽሐፍ» (አል-ኪታብ) እንደ መገለጽ ወይም ራእይ ጠቅሶታል።

ደግሞስ፥ ከመሐመድ በፊትም ሆነ በኋላ፥ አንድ አይሁድ ወይም ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ራእይ ለመለወጥ ለምን ይነሳሳል? ከቶስ ወደ ሲዖል መውረድ ያምረዋልን?

«በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር፥ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።»
(የዮሐንስ ራእይ 22፡ 18-19)

እነዚህ በመሠረቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ጥቅሶች ናቸው። በመጽሐፉ ላይ ለውጥ ተደርጓል ለመባሉ ብቸኛው መንስኤ ያለው «በመጽሐፉ» እና በቁርዓን መካከል ላለው ልዩነት ማብራሪያ ከመስጠቱ ላይ ነው። ሙስሊሞች «መጽሐፉ» ከቁርዓናቸው መጻረሩን ሲገነዘቡ በተቆርቋሪነት መጽሐፍ ቅዱስ የተጭበረበረ መሆን አለበት ወደሚለው ማጠቃለያ ይደርሳሉ።

ከመሐመድ በኋላ በነበሩት በመጀመሪያዎቹ አራት ክፍለ-ዘመናት የጊዜ ገደብ (ከ600-1000 ዓ.ም.) ማንም የእስልምና ትምህርተ-መለኮት ጠቢብ የወንጌሉ ክፍሎች እውነት እንዳልሆኑ አልተከራከረም ነበር። የውሸትነቱን ክስ የጠነሰሰው በ1064 ዓ.ም. በኮርዶባ ላይ የሞተው ኢብን-ቃሲም የሚባል ሰው ነው።



ኢብን-ቃሲም እስልምናን ደግፎ ከክርስቲያኖች ጋር በሚከራከርበት ወቅት በቁርዓንና በወንጌላት መካከል ያሉትን ቅራኔዎች አገኘ። አንዱ ግልጽ ምሣሌ እንዲህ የሚለው የቁርዓን ክፍል ነበር፡- «አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም» (ሱረቱ 4፡ 157)። ኢብን-ቃሲምም «ቁርዓን እውነት መሆን ስላለበት የሚጻረሩት የወንጌል ክፍሎች ውሸት ናቸው» ሲል ተከራከረ። በመቀጠልም «ዳሩ ግን ወንጌሉን እንድናከብር መሐመድ ስለሚናገር፥ አሁን ያለው የወንጌል ክፍል በውሸት የተሞላው በክርስቲያኖች መሆን አለበት» አለ። ይሁን እንጂ መከራከሪያ ነጥቡ በታሪካዊ እውነታዎች የተደገፈ አልነበረም። ይልቁንም የቁርዓንን እውነትነት ለመከለል የተደረገ የእርሱ የብቻው አስተሳሰብና ምኞት ነበር።

በእርግጥ ተደራዳሮዎች ቀድሞ ማጥቃት ከሁሉም የቀለለ መንገድ ይመስላል። «የመጽሐፎቻቸውን ውሸተኛነት ማረጋገጥ ከቻልን ከዚያ ውስጥ የሚያገኙትን የመከራከርያ ነጥቦች ያጣሉ» አለ። ይህም በመጨረሻው የሚከተለውን መግለጫ እንዲጽፍ ገፋፋው። «እግዚአብሔርም እነሱን ይሞግትበት ዘንድ መረጃ አድርጎ ካስቀራቸው ከጥቂቶቹ በቀር ክርስቲያኖች በመጀመሪያ የተገለጠውን ንጹህ የወንጌል ቃል አጥተዋል» አለ።

እንዲያም ሆኖ የአዲስ ኪዳን እውነተኛነት የተቀበሉ በርካታ ታላላቅ የእስልምና ጠበብትም አልታጡም።

የእነዚህም ሰዎች ምስክርነት የክርስቲያን-እስላም ውይይት ኢ.ብን-ቃሲም ባመጣው መሠረተ ቢስ ዘገባ ለዘላለም መታቀብ እንደሌለበት ያረጋግጣል። ሁለቱ ታላላቅ የታሪክ ሰዎች በ956 ዓ.ም. የሞተው አል-ማስኡዲና በ1406 ዓ.ም. የሞተው ኢ.ብን-ካህልዱን የወንጌሉን እውነተኛነት ተቀብለዋል። ሌሎች አራት የታወቁ የሙስሊም የሥነ-መለኮት ጠበብትም ከዚህ ጋር ተስማምተዋል። እነዚህም፡- በ855 ዓ.ም. የሞተው አሊ አት-ታባሪ፥ በ860 ዓ.ም. የሞተው ቃሲም አል-ካሳኒ፥ በ869 ዓ.ም. የሞተው አሞር አል-ጋክሂዝ፥ እና በ1111 ዓ.ም. የሞተው አል-ጋዛሊ ናቸው። ይህንንም አመለካከታቸውን በምዕራቡ ዓለም አቪሲና በመሰኘት ከታወቀውና በ1037 ዓ.ም. ከሞተው አቡ አሊ ሁሴን ኢ.ብን ሲና ጋር ይጋሩታል። የጥንት ባህሎችን በመሰብሰብ ትልቅ ዝና ያተረፈውና በ870 ዓ.ም. የሞተው ቡካሪ «የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውሸት እንዳልታከለበት ለማረጋገጥ ቁርዓን ራሱን ጠቅሷል» ሲሉ ሃንስ ዊጅንጋርድ የተባሉ ጸሐፊ «ወንጌሉን ለማመን እንችላለንን?» በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ገልጸዋል (ሱረቱ 3፡72፥ 78)።



## ቁርአን ስለ ኢየሱስ ምን ይላል?

1. ከድንግል ተወልዷል (ሱረቱ መርየም 19፡16-35)። የአላህን አገላለጽ ልብ በል፡- «ያ ለእኔ ቀላል ነው» (ቁጥር 9)። ይህ በማያሻማ መልኩ አላህ የአባትነት ምሥል እንዳለው ያስረዳል። እባክህ፥ ይህ በሥጋዊ ዓይነት ሁኔታ እንዳልሆነ አስተውል! ይህም በቀጥታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ የሚያስገነዝበው ክርስቲያናዊ አመለካከት ነው።

2. እርሱ መሢሕ ነበር (ሱረቱ ኒሳእ 4፡171)። ቁርዓኑ መሢሕ የሚለውን ቃል አይተረጉመውም። ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለው ትርጉም ተቀባይነትን እንዳገኘ እንገምታለን። የተተነበየውና ተቀባይነት ያገኘው የመሢሑ አገልግሎትም ከኃጢአት ሰውን መቤዠቱ ነበር።

3. እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ መንፈስ ነበር (ሱረቱ ኒሳእ 4፡171)።

4. እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነበር (ሱረቱ ኒሳእ 4፡171)። ይህ ምናልባት «የእግዚአብሔር መገለጽ» ሊባልም ይችላል። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር

የተያያዘ አሳብ ነው (የዮሐንስ ወንጌል 1፡1-14፤ ቆላስዩስ 1፡ 15)።

5. እርሱ አለነቀፋ ነበር (በመሐመድ ማርማዱክ ፒክቶል ትርጉም) ወይም ቅዱስ ነበር (በዩሱፍ አሊ ትርጉም) (ሱረቱ መርየም 19፡19)። ይህ ከማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ነቢይ በተለየና በላቀ ሁኔታ የተነገረለት ነው።

አዳም ኃጢአት ሠርቷል። (ሱረቱ አከ-በቀራህ 2፡36፥ 7፡22፥23)
አብርሃም ኃጢአት ሠርቷል። (ሱረቱ አል-ሹዐራ 26፡81)
ሙሴ ኃጢአት ሠርቷል። (ሱረቱ አል-ቀሶስ 28፡15፥16)
ዮናስ ኃጢአት ሠርቷል። (ሱረቱ አል-ሷፍፋት 37፡142)
ዳዊት ኃጢአት ሠርቷል። (ሱረቱ ሷድ 38፡24፥25)

6. እርሱ በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም እጅጉን የተከበረ ነው። (ሱረቱ አል-ኢምራን 3፡45)

7. እርሱ በእግዚአብሔር ወደ ሰማይ ተወስዷል። (ሱረቱ አል-ኒሳእ 4፡158)



8. እንደገና በዓለም ላይ ሊፈርድ ይመጣል (ሱረቱ አል-ዝኸሩፍ 43፡61 ትርጉም በዩሱፍ አሊ እና ሚሽካት 4፡78-80)።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች በሚፈነጥቁት ብርሃን ብቻ እንኳ፥ ኢየሱስ ተራ ሰው ወይም እንደማንኛውም ያለ ነቢይ እንደሆነ ለመናገር የሚደፍር ሰው ማነው? እንዲህ ያሉ ባሕርያትና ሥነ-ምግባራት ያሉት ነቢይ ከቶ የት አለ?

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ምን ይላል?

ይህ «ኢየሱስ» የሚለው ስም በእርግጥ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት አለብን። ምክንያቱም ይህ ስም በቶራ ውስጥ በትንቢት መነገር ብቻ ሳይሆን፥ በመልአኩ ገብርኤልም በኩል ለማርያም ተሰጥቶአታል። ኢየሱስ የሚለው የአማርኛ ቃል የዕብራይስጡን «የሹዋ» የተካ ቃል ነው። ይህም «ደኅንነት» የሚል ትርጉም ይይዛል። ኢየሱስ አዳኛችን መሆኑን መካድ ማለት እርሱንም በፍጹም መካድ ማለት ነው። ምክንያቱም እርሱን ከአዳኝነቱ ዝቅ ብናደርገው፥ ክብሩን ማዋረዳችን ነውና።

ከ1500-400 ምዕተ ዓመታት ውስጥ የተመዘገበው ብሉይ ኪዳን በበርካታ ምንባቦች ውስጥ የመሚሑን የየሹዋን (የኢየሱስን) መምጣት ተንብዮአል። የኢየሱስን ሕይወትና ትምህርት የሚተርከው አዲስ ኪዳንም እነዚህን ትንቢቶች ሙሉ ለሙሉ ያጠናክራቸዋል።

ይሁን እንጂ ከ89 የወንጌል ምዕራፎች ውስጥ 27 ምዕራፎች (ከሙሉው ወንጌል አንድ ሦስተኛውን ያህል) ምስክርነታቸውን የሰጡበት የወንጌሉ ዋና አሳብ ቁርዓን ውስጥ አለመጠቀሱን (መጥፋቱን) እንመለከታለን። ይህም በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ በመጨረሻ ሳምንት የተፈጸመውንና በመስቀል ላይ መሞቱን የሚገልጽ



ክፍል ነው። ስለሆነም እውነቱን ለማውጣት ደግመን ወደ መረጃዎቹ መመልከት ይኖርብናል።

<u>የዓይን ምስክሮች ዘገባ</u>

እነዚህ ክንውኖች ከማንኛውም የዓይን ምስክር ፊት ርቀው በተከለለ ጥግ ውስጥ በስውር አልተከናወኑም። ይልቁንም በይፋ የተደረጉ ነገሮች በመሆናቸው የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ያውቅ ነበር። ስለሆነም የተጭበረበረ ቢሆን ኖሮ ወንጌሉ በአራት ዘጋቢዎች አማካኝነት በሚዘጋጅበት ጊዜ፥ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በተቃውሞ በተነሳባቸው ነበር። በተቃራኒው ግን ሐዋርያት በተደጋጋሚ በርካታዎቹን የዓይን ምስክሮች እንዲጠይቁ ለሕዝቡ ሲነግሯቸው እንመለከታለን። በዚህ ዓይነት ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት የሚከተለውን ተናግሯል፡-

> «በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉሥ ይህን ነገር ያውቃል፤ ከዚህ ነገር አንዳች እንዳይሰወርበት ተረድቼአለሁና፤ ይህ በስውር የተደረገ አይደለምና።» (የሐዋርያት ሥራ 26፡26)

እንዲሁም ጴጥሮስ ከስቅለቱ በኋላ በጥቂት ቀናት ውስጥ በጴንጠ-ቆስጤ በዓል (በበዓለ ሃምሳ ቀን) ላይ፥ ለበርካታ አይሁዶች የሚከተለውን ተናገረ፡-

> «የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመጸኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳው፤ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና» (የሐዋርያት ሥራ 2፡22-24)።

አይሁዶችም የኢየሱስን በስቅላት መገደል እንዳልካዱ እንመለከታለን። እነርሱ የካዱት መሢሕ መሆኑንና ከሞት መነሣቱን ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጴጥሮስና ሌሎች ጥቂት ሐዋርያት ይህን በማስተማራቸው ከወህኒ ውስጥ ተጨምረዋል። በሸንጎም አቁመዋቸው በአይሁድ ሊቀ ካህናት በተጠየቁ ጊዜም የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡-



> «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል። እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፤ ይህን እግዚአብሔር ለእስራኤል ንስሐን፥ የኃጢአትንም ስርየት ይሰጥ ዘንድ፥ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው። እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው» አሉ። (የሐዋርያት ሥራ 5፡29-32)

እንደዚሁም ጳውሎስ ድርብ መረጃዎችን ያቀርባል። ይኸውም «በመጻሕፍት እንደተጻፈው» ብሎ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን በመጥቀስ እና በርካታ የዓይን ምስክሮችን ማስረጃ በማቅረብ ነው። ከእነዚህም የዓይን ምስክሮች አብዛኞዎቹ በሕይወት ስለነበሩ ሊጠየቁ የሚችሉ ነበሩ። በኋላ ለግሪክ ሰዎች በጻፈላቸው ደብዳቤ ላይ ይህንን ጠቅሰላቸዋል፤ በእስራኤል ውስጥ ግን ስለዚህ መግለጫ መስጠቱ አስፈላጊ አልነበረም።

> «እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ፤ እንዲህ ብዬ፡- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም (ጴጥሮስ) ታየ፤ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙት እስከ

> አሁን አሉ፤ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ፥ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ።» (1 ቆሮንቶስ 15፡3-7)

ይህን አባባል ሐዋርያው ጴጥሮስ ከመገደሉ ጥቂት ቀደም ብሎ በድጋሚ አጽንቶታል። እርሱም የዓይን ምስክሮች ዘገባ እጅግ የጸና መሆኑን ለማጉላት ወደተፈጸመው ትንቢት ያመለክታል። አንድ መስካሪ ሊዋሽ ይችላል። እንዲያውም ብዙ ምስክሮችም ሊዋሹ ይችላሉ። በትንቢትና በፍጻሜው ላይ ግን ምንም ስሕተት ሊኖር አይችልም!

> «የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ፥ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ። ከገናናው ክብር፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ፥ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፤ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን፥ ይህን ድምጽ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን። ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ፥ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ሥፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት



> ሁሉ ማንም ለገዛ እራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» (2ኛ ጴጥሮስ 1፡16-21)

## ታሪክ የወንጌልን እውነት ያጠናክረዋል

ቀደምት የታሪክ ዜናዎችና ዘገባዎች ከጦርነቶች፥ ከታወቁና ከተደነቁ ሰዎች ሕይወት፥ እንዲሁም በጊዜው ከነበሩት መሪዎች በስተቀር እምብዛም ሌላውን ጉዳይ እንደማይዘክሩ ሁላችንም እናውቃለን። እንዲህም ስለሆነ እንደ ገሊላና ይሁዳ በመሳሰሉ የገጠር ከተሞች የሚፈጸሙ ድርጊቶች የታሪክ ዕይታ ያገኛሉ ብሎ መገመትም ያስቸግራል። ቢደረግም እንኳ ትኩረት የሚሰጣቸው የጦርነትና የንጉሣውያን ቤተሰቦች ጉዳዮች ናቸው። ይህም ቢሆን ግን የመጽሐፍ ቅዱስን ዘገባ የሚደግፉ ማጣቀሻዎች አልታጡም።

ቆርኔሌዎስ ታክቱስ የሮማ መንግሥት ታላቁ የታሪክ ሰው ነበር። እርሱም ክርስቲያኖች ስለ «ወንጀሎቻቸው» በሮማ ነዋሪዎች እንዴት እንደተጠሉና በ64 ዓ.ም. ኔሮ ሮምን በእሳት አጋይቷት የገዛ ጥፋቱን ግን በእነርሱ ላይ አላክኮ እንዳስቀጣቸው ይተርካል።

ታክቱስ እንዲህ በማለት ይጽፋል:- «ክርስቲያን የሚለው ስም» የመጣው በጢባሪዮስ ዘመነ-መንግሥት በጴንጤናዊው ጲላጦስ ከተገደለው ከክርስቶስ ነው። ለጥቂት ጊዜ የታገደውም ይህ አደገኛና መሠረተ-ቢስ እምነት፥ እንደ አዲስ ተቀጣጥሎ የበሽታው ምንጭ በሆነችው በይሁዳ ብቻ ሳይወሰን፥ ርኩስ የሆነ ነገር ሁሉ ከያቅጣጫው እየመጣ አድናቆት በሚያተርፍባት በሮምም ሳይቀር ተሰራጭቷል።»

በወቅቱ የክርስቲያን ኃይማኖት ከባለጠጎች ይልቅ ጎልቶ ይታይ የነበረው በአጠቃላይ በዝቅተኞቹ የኅብረተሰብ ክፍሎችና በተለይም ከእስራኤል በስተ ምሥራቅ በሚኖሩት ሕዝቦች ዘንድ ስለነበር፥ ታክቱስ ለክርስትና ተቆርቋሪ ሰው እንዳልነበር ግልጽ ነው። ስለሆነም ከእርሱ የተገኘው መረጃ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚጠራጠሩ ከሁሉም በላይ ተቀባይነት ያለው ነው። («ረንአዌይ ወርልድ» በማይከል ግሪን)።

በ70 ዓ.ም. በሮም መንግሥት ላይ የተቀሰቀሰው የአይሁዶች ዓመፅ መሪዎች መካከል ጆሲፈስ አንዱ ነበር። እርሱም «አንቲኩቴትስ ዩጼይካይ» (93 ዓ.ም.) እና «ዲ ቤሎ ዩጼይካይ» (75-79 ዓ.ም.) በሚባሉ ጽሑፎች ውስጥ ለሮማ ሕዝብ የአባቶቹን ሃይማኖት ለማሳወቅ ጽፎአል። በነዚህም ውስጥ ብዙ በአዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ የምናውቃቸውን ዋና ዋና ባለ ታሪኮች:- እነ ጲላጦስን፥ ሐናንያን፥ ቀያፋን፥



ሄሮድስን፥ ቄሬኔዎስ፥ ፊልክስን፥ ፊስጦስንና ሌሎችንም ተገልጸው እናገኛለን። እንደዚሁም ደግሞ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ጽፎአል፤ ስብከቱን፥ ጥምቀቱንና መገደሉንም ዘግቦአል። ዳሩ ግን ከሁሉም የሚበልጠው፥ ስለ ኢየሱስ የጠቀሰው ጉዳይ ነው። እንዲህም ተብሎ ይነበባል:-

«በዚያን ጊዜ ኢየሱስ የሚባል ጠቢብ ሰው ነበር። ሰው ነው ማለቱ እንኳ አግባብ አይደለም። እርሱም የድንቅ ሥራዎች አድራጊና ለብዙዎቹ እውነትን በቅንነት ያስተማረ መምህር ነበር። እርሱም በርካታ አይሁዶችንና አሕዛብን ወደ እራሱ ስቧል። እርሱ ክርስቶስ (መሲሕ) ነበር። ጲላጦስም በዋነኞቻችን ምክር ለመስቀል ሞት አሳልፎ በሰጠው ጊዜ፥ በመጀመሪያ የወደዱት ወዳጆቹ አልተለዩትም ነበር። ምክንያቱም በሦስተኛው ቀን ሕያው ሆኖ ተገልጦላቸው ነበርና ነው። እርሱን በተመለከተ ይህንንና ሌሎች አሥር ሺህ የሚሆኑ ድንቅ ነገሮችን ቅዱሳን ነቢያት ተንብየው እንደነበረው ተፈጸመ። እንደዚሁም፥ ስያሜውን ከእርሱ ያገኘው የክርስቲያኖች ነገድም በዚህ ዘመን ሊጠፋ አልተቻለም።» («አንቲኩቴትስ ዩዳይካይ» ቅጽ 18፥111:3)።

## የተፈጸመው ትንቢት የወንጌሉን እውነት ያጠናክረዋል

ሁላችንም ስለ ኢየሱስ ተአምራት እናውቃለን። በ «ሚሽካት» ውስጥ ተአምራትን በሚያስተዋውቅበት ጊዜ፥ አል-ሃጅ መውሌና ፋዝሉል ካሪም የሚከተለውን በትክክል አስቀምጧል፡-

«በተአምራት ውስጥ እጅግ ትልቁ ነገር ትንቢት ነው። ይህም ማለት ሊሆኑ ስላላቸው የወደፊት ነገሮች ገልጦ መናገር ማለት ነው። ይህም ከመለኮታዊ እውቀት የመነጨ የመጪውን ዘመን ምሥጢር ትንበያ እንጂ ተራ የፖለቲካ መላ-ምት አይደለም። ትንቢት በሚከተሉት ምክንያቶች ከሁሉም የላቀ ነው። ትንቢት በታሪክ ሊረጋገጥ ሲችል፥ ተአምር ግን አይችልም። ትንቢት እግዚአብሔር ገና በሩቅ ስላለው ነገር እንደሚያውቅ ሲያመለክት፥ ተአምር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል ያሳያል። ስለሆነም እውቀት ከኃይል እንደሚበልጥ ሁሉ ትንቢትም ከተአምር ይበልጣል።»

ማቴዎስ በጻፈው ወንጌል ውስጥ ብቻ እንኳን፥ ከ60 የማያንሱ ማጣቀሻዎች ስለ ተፈጸሙት ትንቢቶች ተገልጸዋል። ይህን ለማረጋገጥ ጥቂት የተመረጡ ጥቅሶች ከዚህ መጽሐፍና ከሌሎችም ቀጥለው



ይቀርባሉ።

ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት በ700 ዓ.ዓ. አካባቢ ስለ ኢየሱስ የትውልድ ቦታና ቅድመ-ሕላዌ የተነገረ ትንቢት፡-

«አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።» (ሚክያስ 5:2)።

ፍጻሜው፡-

«ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለነበረ፥ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ። በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ፤ የበኩር ልጅዋንም ወለደች፤ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ሥፍራ ስላልነበራቸው፥ በግርግም አስተኛችው።» (የሉቃስ ወንጌል 2:4-7)።

ድንግል እንደምትወልድ፥ ስለ ኢየሱስ
መለኮታዊነትና የተለየ ልጅነት በ700 ዓ.ዓ.
አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) ብላ ትጠራዋለች።» (ትንቢተ ኢሳይያስ 7፡14)።

«ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» (ትንቢተ ኢሳይያስ 9፡6)።

ፍጻሜው፡-

«የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበር። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ፥ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ፥ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፤ እንዲህም አለ፡- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን



ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፥ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፤ ትርጓሜውም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።» (ማቴ. 1፡18-23)። ይህም በብዙ የቁርዓን የምንባብ ክፍሎች የተደገፈ ነው።

ኢየሱስ የሚመጣበት ጊዜ መቼ እንደሆነ በነቢዩ ዳንኤል ከምዕራፍ 9፡24 ጀምሮ በ500 ዓ.ዓ. አካባቢ ትንቢት ተነግሮአል። ይህ ምንባብ ለዚህ ዓይነቱ አነስተኛ መጽሐፍ የተወሳሰበ ስለሆነ ለማብራራት ከመሞከር ተቆጥበናል።

ለማዳንና ለመፈወስ እንደሚመጣ በ700 ዓ.ዓ.
የተነገረ ትንቢት፡-

«እነሆ፥ አምላካችሁ በበቀል በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና፥ መጥቶም ያድናችኋልና በርቱ፤ አትፍሩ በሉአቸው። በዚያን ጊዜም የዕውሮች ዓይን ይገለጣል፤ የደንቆሮችም ጆሮ ይከፈታል።» (ትንቢተ ኢሳይያስ 35፡4፥5)።

ፍጻሜው፡-

ሀ/ ለማዳን መጣ።

«እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።» (ማቴዎስ 1፡21)።

«የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና።» (ሉቃስ 19፡10)።

«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፤ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ፥ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፡ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ



የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።» (ዮሐንስ 3፡13-21)።

«አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፤ እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና፥ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል፥ እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ፥ በደሙም የሆነ ማስተሰሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፤ እራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው።» (ሮሜ 3፡21-26)።

«እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን፥ በእግዚአብሔር ዘንድ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤

በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን።» (ሮሜ 5፡1-2)።

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶናልና።» (ሮሜ 8፡1-2)።

ለ/ ለመፈወስ መጣ።

«ኢየሱስም ቆሞ ወደ እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ። በቀረበም ጊዜ፡- ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? ብሎ ጠየቀው። እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አይ ዘንድ ነው አለ። ኢየሱስም፡- እይ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። በዚያን ጊዜም አየ፤ እግዚአብሔርንም እያከበረ ተከተለው። ሕዝቡም ሁሉ አይተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።» (ሉቃስ 18፡40-43)።

«ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር። ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ፤ በልዩ ልዩ ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም ያደሩባቸውን፥ በጨረቃም



የሚነሳባቸውን፥ ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ፤ ፈወሳቸውም።» (ማቴዎስ 4፡23-24)።

«ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከና፡- የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ? አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ሄዳችሁ ያያችሁትን፥ የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምጻሞችም ይነጻሉ፤ ደንቆሮችም ይሰማሉ፤ ሙታንም ይነሳሉ፤ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው።» (ማቴዎስ 11፡2-6)።

«በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ። በነቢዩ በኢሳይያስ፡- እርሱ ድካማችንን ተቀበለ፤ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፤ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ።» (ማቴዎስ 8፡16-17)።

«እነሆም ኢያኢሮስ የሚባል ሰው መጣ፤ እርሱም የምኩራብ አለቃ ነበር፤ በኢየሱስም እግር ላይ ወድቆ ወደ ቤቱ እንዲገባ ለመነው፤ አሥራ ሁለት ዓመት የሆናት አንዲት ሴት ልጅ ነበረችውና፤ እርስዋም ለሞት ቀርባ ነበረች። ... እርሱም ገና

ሲናገር፥ አንድ ሰው ከምኩራብ አለቃው ቤት መጥቶ፡- ልጅህ ሞታለች፤ እንግዲህ መምህሩን አታድክም አለ። ኢየሱስ ግን ሰምቶ፡- አትፍራ፤ እመን ብቻ፤ ትድንማለች ብሎ መለሰለት። ወደ ቤትም ሲገባ ... ሁሉም እያለቀሱላት ዋይ ዋይ ይሉ ነበር። እርሱ ግን፡- አታልቅሱ፤ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም አለ። እንደሞተችም አውቀው በጣም ሳቁበት። እርሱ ግን እጅዋን ይዞ፡- አንቺ ብላቴና፥ ተነሺ ብሎ ጮኸ። ነፍስዋም ተመለሰች፤ ፈጥናም ቆመች ...» (ሉቃስ 8፡41-42፥49-55፤ በተጨማሪም ሉቃስ 7፡1-10 አንብብ)።

## በ700 ዓ.ዓ. አካባቢ ስለ ኢየሱስ ስም የተነገረ ትንቢት፡-

«ደሴቶች ሆይ፥ ስሙኝ፤ እናንተም በሩቅ ያላችሁ አሕዛብ፥ አድምጡ፤ እግዚአብሔር ከማኅፀን ጠርቶኛል፤ ከእናቴም ሆድ ጀምሮ ስሜን አንሥቶአል፤ አፌንም እንደተሳለ ሰይፍ አድርጎአል ... እስከ ምድረ በዳ ድረስ መድኃኒት (ይህም በዕብራይስጥ የሹዋ ማለት ሲሆን፥ በእስራኤል አገር በኖረበት ዘመን ኢየሱስ ይጠራበት የነበረው ስም ነው) ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል።



የእስራኤል ታዳጊ ቅዱስም፥ እግዚአብሔር፥ ሰዎች ለሚንቁት፥ ሕዝብም ለሚጠላው፥ ለገዢዎች ባሪያ እንዲህ ይላል ...» (ኢሳይያስ 49፡1-7፤ በተጨማሪም ኢሳይያስ 12፡2፥3ን ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር እያመሳከርህ ተመልከት፡- ዮሐንስ 7፡37፤ 4፡10-14፤ የዮሐንስ ራእይ 21፡6፤ ኢሳይያስ 52፡10 ወዘተ.)።

ፍጻሜው፡-

መልአኩ ለዮሴፍ እንዲህ አለው፡-

«ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።» (ማቴዎስ 1፡21)

ምናልባት በኢሳይያስ ላይ የተጠቀሰው ትንቢት የኢየሱስን አምላክነትና ልጅነት ከማመልከቱ ላይ ሙስሊሞች ክርክር ያስነሱ ይሆናል እንጂ፥ እስከዚህ ነጥብ ድረስ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሊስማሙ ይችላሉ። ቢሆንም የእርሱን አምላክነት የሚገልጹ ትንቢቶችና ፍጻሜአቸውን መመልከት አለብን።

አስተውል፡- ስለሌላ ስለማንም ሰው እንደሚከተለው ሊነገር አይችልም፡-

1. እርሱ እንዲህ ባለ አስደናቂ ሁኔታ ተወልዷል፤

3. ክፉ መናፍስትን አስወጥቷል፤

4. እርሱ ኃጢአት ያልነካው ቅዱስ ነበር (ሱረቱ 19፡19፤ ዕብራውያን 4፡15፤ 1 ዮሐንስ 3፡5፤ 2 ቆሮንቶስ 5፡21፤ 1 ጴጥሮስ 2፡22፤ ትንቢተ ኢሳይያስ 53፡9፥ ወዘተ.)፤

5. እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ሱረቱ 4፡171፤ ዮሐንስ 1፡1፤ 2፡14)፤

6. እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ መንፈስ ነበር (ሱረቱ 4፡171)፤

7. በተግባር ከመፈጸማቸው ከብዙ ዓመታት ቀደም ብሎ ስለ ኢየሱስ ሕይወት ከላይ ያየናቸውን የመሳሰሉ ትንቢቶች በዝርዝር ተነግረው ነበር።

አሁን ደግሞ ስለ ኢየሱስ የሕይወት ፍጻሜ በብሉይ ኪዳን የተተነበየውንና ፍጻሜውን እንመለከታለን።

ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ በትሕትና
ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ በ480 ዓ.ዓ.
አካባቢ የተነገረ ትንቢት፤



«አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥ እልል በዪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያዪቱ ግልገል በውርንጫዪቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል።» (ዘካርያስ 9፡9)።

ፍጻሜው፡-

«ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው፥ ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፤ እንዲህም አላቸው፡- በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፤ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ፥ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁም አምጡልኝ። ማንም አንዳች ቢላችሁ፡- ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያም ይሰዳቸዋል። ለጽዮን ልጅ፡- እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያዪቱ ግልገል በውርንጫዪቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።

«ደቀ መዛምርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ አህያዪቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፤ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፤ ተቀመጠባቸውም። ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎችም

ከዛፍ ጫፍ ጫፉን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር። የሚቀድሙትም ሕዝብ የሚከተሉትም፡- ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፥ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር።» (ማቴዎስ 21፡ 1-9)።

ስለ ኢየሱስ አልፎ መስጠት በ 1000 ዓ.ዓ. አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«ደግሞ የሰላሜ ሰው የታመንሁበት ... በእኔ ላይ ተረከዙን አነሳ» [መዝሙር (41)፡ 9]።

በ480 ዓ.ዓ. አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«እኔም፡- ደስ ብሎአችሁ እንደሆነ ዋጋዬን ስጡኝ፤ ያለዚያ ግን ተዉት አልሁ። እነርሱም ለዋጋዬ ሠላሳ ብር መዘኑ። እግዚአብሔርም፡- የተስማሙበትን የከበረውን ዋጋዬን በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑረው አለኝ። እኔም ሠላሳውን ብር (ይህም የባሪያ ዋጋ ነው) ወስጄ በእግዚአብሔር ቤት ባለው በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኖርሁት።» (ዘካርያስ 11፡ 12-13)።



ፍጻሜው፡-

«ከአሥራ ሁለቱም አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ወደ ካህናት አለቆች ሄደ። ሲሰሙም ደስ አላቸው፤ ብርም ይሰጡት ዘንድ ተስፋ ሰጡት። በሚመች ጊዜም እንዴት አድርጎ አሳልፎ እንዲሰጠው ይፈልግ ነበር።

«በመሸም ጊዜ፥ ከአሥራ ሁለቱም ጋር መጣ። ተቀምጠውም ሲበሉ ኢየሱስ፡- እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ፥ እርሱም ከእኔ ጋር የሚበላው አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። እነርሱም እያዘኑ፥ እያንዳንዳቸውም፡- እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር። እርሱም መልሶ፡- ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ከእኔ ጋር ወደ ወጭቱ እጁን የሚያጠልቀው ነው። የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ውዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አላቸው።»

«ወዲያውም ገና ሲናገር፥ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፤ ከእርሱም ጋር ብዙ ሰዎች ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከጻፎች ከሽማግሌዎችም ዘንድ መጡ። አሳልፎ የሚሰጠውም፡- የምስመው እርሱ ነው፤ ያዙት፤ ተጠንቅቃችሁም ውሰዱት ብሎ ምልክት

ሳመው፤ እነርሱም እጃቸውን በእርሱ ላይ ጭነው ያዙት።» (ማርቆስ 14፡10-11፥ 17-21፥ 43-46)።

«በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፤ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሎች መልሶ፡- ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን፡- እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ። ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ። የካህናት አለቆችም ብሩን አንስተው፡- የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ። ተማክረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት። ስለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ።» (ማቴዎስ 27፡3-8)።

በ 700 ዓ.ዓ. አካባቢ ስለ ኢየሱስ ሥቃይና የመስቀል ሞት የተነገረ ትንቢት፡-

«... መልክና ውበት የለውም፤ ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ፥ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም



የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፤ እኛም አላከበርነውም።

«በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደተመታ፥ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ፥ እንደተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቀበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

«ተጨነቀ፤ ተሠቃየም፤ አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ (በሁለት ወንበዴዎች መካከል ተሰቅሏል)፤ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ (በባለጸጋ ሰው መቃብር ውስጥ ተቀብሯል)፤ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር።

«እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ። ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፤ ዕድሜውም ይረዝማል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፤ ደስም ይለዋል። ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን (ሁሉንም አይደለም) ያጸድቃል፤ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፤ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።» (ትንቢተ ኢሳይያስ 53)።

በ1000 ዓ.ዓ. አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ። ... የሚያዩኝ ሁሉ ይላገጡብኛል፤ ራሳቸውን እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ፡- በእግዚአብሔር ተማመነ፤ እርሱንም ያድነው፤ ቢወድደውስ ያድነው። አንተ ግን ከሆድ አውጥተኸኛልና፥ በእናቴ ጡት ሳለሁም በአንተ ታመንሁ።



«እንደ ነጣቂና እንደሚጮህ አንበሳ በላዩ አፋቸውን ከፈቱ። እንደ ውኃ ፈሰስሁ፤ አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ፤ ልቤ እንደ ሰም ሆነ፤ በአንጀቴም መካከል ቀለጠ። ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ፤ በጉሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ፤ ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ። ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፉተኞች ጉባዔም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ፤ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።» [መዝሙር (22)፡ 1፥ 7-9፥ 13-18]።

ፍጻሜው፡-

«ኢየሱስም መልሶ፡- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው። ጲላጦስም፡- እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ ንጉሥ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ፤ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። ጲላጦስ እውነት ምንድር ነው? አለው። ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ፡- እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም። ነገር ግን በፋሲካ

አንድ ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤ እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን? አላቸው። ሁሉም ደግመው፦ በርባንን እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ ነበር።» (ዮሐንስ 18፡36-40)።

«በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው። ወታደሮችም ከእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ፤ ቀይ ልብስም አለበሱት፤ እየቀረቡም፦ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር፤ በጥፊ ይመቱት ነበር። ጲላጦስም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ፦ እነሆ፥ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ፥ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው። ኢየሱስም የእሾህ አክሊል ደፍቶ፥ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ። ጲላጦስም፦ እነሆ ሰውዬው አላቸው።

«የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ፦ ስቀለው ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም፦ እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት አላቸው።

«አይሁድም መለሰው፦ እኛ ሕግ አለን፤ እንደ ሕጋችን ሊሞት ይገባዋል፤ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና አሉት። ስለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ፈራ፤ ተመልሶም ወደ ገዡ



ግቢ ገባና ኢየሱስን፦ አንተ ከወዴት ነህ? አለው። ኢየሱስ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም። ስለዚህ ጲላጦስ፦ አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው። ኢየሱስም መለሰ፦ ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።

«ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ፤ ነገር ግን አይሁድ፦ ይህንስ ብትፈታው የቄሳር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሳር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ጲላጦስን ወደ ውጭ አወጣው፤ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለው ጸፍጸፍ በሚሉት ሥፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ። ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበር፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም፦ እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው። እነርሱ ግን፦ አስወግደው፤ አስወግደው፤ ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም፦ ንጉሣችሁን ልስቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም፦ ከቄሳር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት። ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።

«ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ

ቅል ሥፍራ ወደሚሉት ወጣ። በዚያም ሰቀሉት፤ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት፥ አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ፥ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉ። ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም:- የአይሁድ ንጉሥ፤ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበር። ኢየሱስም የተሰቀለበት ሥፍራ ለከተማ ቅርብ ነበረና፥ ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡት፤ በዕብራይስጥና በሮማይስጥ፥ በግሪክም ተጽፎ ነበር። ስለዚህ የአይሁድ ካህናት አለቆች ጲላጦስን:- እርሱ:- የአይሁድ ንጉሥ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ አሉት። ጲላጦስም:- የጻፍሁትን ጽፌአለሁ ብሎ መለሰ።

«ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ፥ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት፤ እጀ ጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም። ስለዚህ እርስ በእርሳቸው:- ለማን እንዲሆን በእርሱ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ። ይህም:- ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ፤ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።



«ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል ላይ እናቱ፥ የእናቱም እህት፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን:- አንቺ ሴት፥ እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን:- እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።

«ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ:- ተጠማሁ አለ። በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው እንዲጠጣ አቀረቡለት። ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ:- ተፈጸመ አለ፤ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።

«አይሁድም የማዘጋጀት ቀን ስለሆነ ያ ሰንበት ትልቅ ነበርና ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር፥ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው ጲላጦስን ለመኑት። ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን፥ ከእርሱ ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤ ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤ ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ

ወጣ። ያየውም መስክሮአል፤ ምስክሩም እውነት ነው፤ እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል። ይህም የሆነ፡- ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው። ደግሞም ሌላው መጽሐፍ፡- የወጉትን ያዩታል ይላል።» (ዮሐንስ 19፡ 1-37)።

ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ በ1000 ዓ.ዓ. አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ፤ በቀኜ ነውና አልታወክም። ስለዚህም ልቤን ደስ አለው፤ ምላሴም ሐሤት አደረገች፤ ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች፤ ነፍሴም በሲኦል (ከምድር በታች፥ በመቃብር) አትተዋትምና ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።» [መዝሙር (16)፡ 8-10]።

ፍጻሜው፡-

«ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ። ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት፤ ገብተውም የጌታን



የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ፥ እነሆ፥ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ፤ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፥ እንዲህ አሉአቸው፡- ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም። የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል፥ በሦስተኛውም ቀን ሊነሳ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደተናገረ አስቡ። ቃሎቹንም አሰቡ፤ ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለሌሎች ነገሩአቸው። ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና፥ የያዕቆብም እናት ማርያም፥ ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። ይህም ቃል ቅዠት መስሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም።» (ሉቃስ 24፡ 1-11)።

ስለዕርገቱ በ1000 ዓ.ዓ. አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«እግዚአብሔር ጌታዬን፡- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።» [መዝ. (110)፡ 1]።

ፍጻሜው፡-

«እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፡- ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት። እርሱም፡- አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም፡- የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።» (የሐዋርያት 1፡6-11)።

ገናም ያልተፈጸመ ትንቢት ስለ እስራኤል መጸጸትና ወደ ኢየሱስ መመለስ በ480 ዓ.ዓ. አካባቢ ተተንብዮ ገና ያልተፈጸመ ትንቢት፡-

«በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፥ የምገስንና የልመናን (የጸሎትን) መንፈስ



አፈስሳለሁ፤ ወደ እነርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፤ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፤ ሰውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን፥ በመራራ ኃዘን ያዝኑለታል።» (ዘካርያስ 12፡10)።

እግዚአብሔር ወልድ የሆነውን ኢየሱስን ከእግዚአብሔር አብ ነጥለው ለማየት የሚወዱትን የዘመናችንን ሰዎች ሁኔታ የሚያመለክት በ1000 ዓ.ዓ. አካባቢ የተነገረ ትንቢት፡-

«የምድር ነገሥታት ተነሡ፤ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ (መሢሑም የተቀባው፥ ክርስቶስ ነው) እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፡- ማሰሪያቸውን እንበጥስ፤ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል ... ትዕዛዙን እናገራለሁ፤ እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፤ (እባክህ ይህ ሥጋዊ አገላለጽ እንዳልሆነ ልብ በል)፤ እኔ ዛሬ ወለድሁህ። ለምነኝ፤ አሕዛብን ለርስትህ፥ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ።» (መዝሙር 2፡2-8)።

«የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።» (ማቴዎስ 20፡28)።

«ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» (ማቴዎስ 26፡28)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ፥ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፥ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» (ዮሐንስ 3፡16)።

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ ... እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም።» (ዮሐንስ 10፡11፥ 15፥ 18)

በዓለም ካሉት ኢቃቂር አውጪዎች መካከል አንዱም እንኳን እነዚህ ተፈጻሚነት ያገኙትን ትንቢታዊ መረጃዎች ዋጋ ሊያሳጣ የሚችል ምንም ዓይነት ዘገባ ሊያቀርብ አይችልም። ይህ በታሪክ ሁሉ የተለየና ለሌሎችም የሃይማኖት መጻሕፍት እንግዳ የሆነ ነገር ነው። እግዚአብሔር እንደድርና ማግ እርስ በርሱ የተስማማውን መልእክቱን ለሰው ልጆች ሁሉ ሲሰጥ የገዛ ማኅተሙን አኑሮበታል። ስለዚህም ማንኛውም ቅን የሆነና እውነትን የሚሻ አንባቢ ይህን እውነት ማረጋገጥ



አይቸግረውም። ይኼውም መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ሃይማኖተኞች የገዛ አስተሳሰባቸውን በሌሎች ጫንቃ ላይ ለመጫን ሲሉ የጻፉት ልብ ወለድ አለመሆኑን ነው። ከላይ የቀረበውን መረጃ በማስተዋል የመረመረ ማንም ሰው ቢሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቷል ወይም ተበርዟል ብሎ ሊናገር ከቶ አይደፍርም!

እንግዲህ ምናልባት ብሉይ ኪዳን በከፊልም ቢሆን ይህንኑ ትንቢት ለማስገኘት ሲባል ከአዲስ ኪዳን በኋላ ተጽፎ ይሆን? ይህ ከብዙ ምክንያቶች የተነሳ በፍጹም የማይታሰብ ጉዳይ ነው። አይሁዶች ቅዱሳት መጻሕፍትን እጅግ ንቅተውና ተንከባክበው ይጠብቁአቸው ነበር። እነርሱ ራሳቸውም ከራሳቸው እምነትና ልምምድ ጋር ስለሚጋጩባቸው እነዚህ ትንቢቶች በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ እንዲኖሩ አይወዱም ነበር። ለዚህም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አብዛኛዎቹ ምንባቦች በየሰንበቱ በሚቀርበው የምንባብ ክፍለ ጊዜ ላይ በማንኛውም ምኩራብ ውስጥ ተነበው አለማወቃቸው በአስረጅነት ይጠቀሳል። ከዚህም በተጨማሪ፥ ብሉይ ኪዳን ከክርስቶስ ልደት በፊት በስፋት የተሠራጨ ሲሆን ከ 300-200 ዓ.ዓ. አካባቢ ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ግሪክ ተተርጉሞአል። ስለሆነም በስፋት የተሠራጨውን መጽሐፍ መልሶ «መከለስ» በፍጹም የማይቻል ነገር ነው። ደግሞም

እነዚህን ትንቢቶች የያዙ፥ ከክርስትና በፊት የነበሩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከእጃችን አሉ።

## ማጠቃለያ

1. የዓይን ምስክሮች፥ የታሪክ ዘጋቢዎችና የተፈጸሙ ትንቢቶች መረጃ የአንድን ሰው አስተሳሰብ ወይም ተስፋ የማያሟሉ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ ወደጎን ገሸሽ አድርጎ መተው አይገባም።

2. መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቷል የሚለው ማስተባበያ፥ መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ቁርአንንም ጭምር ከተሳሳተ አተረጓጎም ላይ የሚጥል ከፉ የስም ማጥፊያ ዘመቻ ነው። ይህም ከሐሰተኛ አመለካከትና እንዲሁም ጥቃቅን የቅጂዎች ስሕተቶችን ያለ ቅጥ ከማጉላት የመነጨ ነው። ቁርዓንም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የመመርመር ዕድል ቢገጥመው፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ እርሱንም ለመቀመር የሰው እጆች ድርሻ ምን ያህል እንደነበረ ለማወቅ ይቻላል።

3. መረጃዎቹ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ የተናገረውን ሁሉ ይደግፋሉ። ይህም ማለት ኢየሱስ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ባለመብቃቱ ምክንያት ወደ ዘላለማዊ ጨለማ እንዳይጣል ከእግዚአብሔር የተላከ ብቸኛው መለኮታዊ የደኅንነት መንገድ መሆኑ ነው። በራሳችን ስግብግብ አሳብና አድራጎት ሁላችንም እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን እቅድ ተላልፈናል። በመሆኑም ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ሆነዋል። እግዚአብሔር በክብሩ ባለበት ሥፍራ ለመድረስም ሁላችንም ይቅርታን መፈለግ አለብን። ራሱንም ንጹሕ አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም የሚችል ማንም የለም። ማንም ቢሆን መልካም ሰው ለመሆን በመጣሩ በፊት የሰራውን ኃጢአት ሊያስተሰርይ አይችልም። ደግሞም የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ይቅርታን ሳይጠይቅ ማንም ይቅር ሊባል አይችልም። እንደ ቶራና ወንጌል አገላለጽ፥ ቅጣቱ በኢየሱስ ላይ እስካልተፈጸመ ድረስ ይቅርታ ሊገኝ አይችልም። ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና ለመድረስ ብቸኛው መንገዳችን እርሱ ነው። ለዘላለምም ሕይወት ብቸኛው ተስፋችን እርሱ ነው።

ማንም በጎ ሕሊና እና የእግዚአብሔር ፍቅር ያለው ሰው እነዚህን ሁሉ ድንቅ ማስረጃዎች ሳይመረምር፥ በቸልታ አያልፍም። ማንኛውም የሰው ማጥላላት ወይም ስደት በመረጃ የበለጸገውን የእግዚአብሔርን እውነትና የይቅርታ ስጦታ እንድንተው ሊገፋፋን አይገባም። ምህረትና የዘላለም ሕይወትም ከእርሱ ዘንድ ናቸውና!

በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ በማመሳከሪያነት የተጠቀሱት ምንባቦች ሁሉ እጅግ የተወሳሰቡ ይሆኑብዎት ይሆናል።

ለተጨማሪ ማብራሪያ በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ፡-

የሕይወት በር

መ.ሣ.ቁ. 4937

አዲስ አበባ